# "እስከ መጨረሻው የሚጸና ግን እሱ ይድናል"

ከብፁዕ አባ ገብርኤል ሊቀጳጳስ

የዐቢይ ጾም አምስተኛው እሑድ በቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት "ደብረ ዘይት ተብሎ ይጠራል። በግዕዝ ልሣን ደብረዘይት ማለት የወይራ ተራራ ማለት ነው። ተራራው ወይራ የበዛበት ስለነበር ደብረ ዘይት ተባለ። ብዙ ጊዜ በደብረ ዘይት እየተገኘ ትምህርት ይሰጥ ነበር። በወንጌሉ እንደ ተጻፈ መድኃኒታችን ዕለት በዕለት በመቅደስ እየተገኘ ያስተምር ነበር፤ ሌሊት ሌሊት ግን ደብረ ዘይት ወደሚባል ተራራ ወጥቶ ያድር ነበር ተብሎ ተመልክቶአል። (ሉቃስ 21፥37)

በዚያ ልማድ መሠረት ጌታችን ዓለምን ለማሳለፍ ደግሞ የሚመጣበትን ምልክትና ጠቋሚ ነገር ምን ምን እንደሆነ፣ እሱ ከመምጣቱ በፊት በዓለም ላይ ምን፥ ምን እንደሚደረግና ምን እንደሚታይ ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው በደብረ ዘይት ተራራ ላይ ተቀምጦ ነው። (ማቴ.24፥1-51) ስለ ዓለም ሁሉ ቤዛ ለመሆን በሚሰቀልበት ቀን ዋዜማ ማለት በትልቁ ሐሙስ (ጸሎተ ሐሙስ) በለበሰው ሥጋ የጸለየው ከደብረ ዘይት ጋር ተያይዞ በሚገኘው ቦታ በጌተሴማኒ ነበር። (ማቴ.26፥36) በኃላ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላም ለደቀመዛሙርቱ እንዲነግሩ ሲልካቸው፥ "ሂዱና ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፥ በዚያም ታዩኛላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው፥" ብሎ የላካቸው በደብረ ዘይት ገሊላ ተብላ ትጠራ ወደ ነበረችው ቦታ ነው። (ማቴ.28፥9) ገሊላውያን ወደ ኤየሩሳሌም ሲመጡ በደብረ ዘይት ያርፍ ነበርና እነሱ ሲያርፉባት የነበረችው ቦታ ገሊላ እየተባለች ትጠራ ነበር። መድኃኔዓለም ክርስቶስ የድኅነት ሥራ ፈጽሞ ወደ ሰማይ ያረገው ከዚህ ተራራ ተነሥቶ ነው። (ሐዋ,1፥12) ቀደም ብሎም የሆሳዕናው የመድኃኔዓለም አስደናቂ ጉዞ የተጀመረው ከደብረ ዘይት ሥር ነበር። (ማቴ.21፥1-16)

የጌታችን ደቀመዛሙርት ከጌታችን ጋር ሆነው አይተውና ጎብኝተው በሚመጡበት ጊዜ የቤተ መቅድሱን ሕንጻ የሕንጻ ማማር አንሥተው ለጌታችን ሊያወሩለት ጀመሩ። ጌታችን ግን፥ "ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም፥" ሲል መለሰላቸው። (ማቴ.24፥1)

ከዚያ በኋላ መድኃኔዓለም ክርስቶስ በደብረዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፥ "ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው?" አሉት። እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው፦ "ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፤

1ኛ) ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉ። ብዙዎችንም ያስታሉ።

2ኛ) ጦርነትን የጦርነትም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ። ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፤ አትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።

3ኛ) ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥት በመንግሥት ላይ ይነሣል፤

4ኛ) ራብ፥ ቸነፈር፥ የምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ የምጥ ጣር (የመከራ) መጀመሪያ ናቸው።

5ኛ) በዚያን ጊዜ ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ ብዙዎችም እርስ በራሳቸው ይሰጣጣሉ፤ እርስ በርሳቸው ይጣላሉ።

6ኛ) በዚያን ጊዜ ብዙ ሐሰተኛ ነቢያት ይነሣሉ። ብዙዎችንም ያስታሉ።

7ኛ) በዚያን ጊዜ በዓመፅም ብዛት (ከሐሰትም ብዛት) የተነሣ <u>የብዙዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። ነገር ግን እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።</u> ከዚያም ለዓለም ሁሉ ምስክር እንዲሆን (ለዓለም ምስክር እንዲሆንበት) የመንግሥተ ሰማያት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜ መጨረሻው ይመጣል። እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለው የጥፋት ርኵሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ አንባቢው (ሰባኪው) ያስተውል፥" ብሎ ጌታችን ለቀደመዛሙርቱ ነገራቸው።(ማቴ.24፥5-17)

ከዚህ በላይ እንዳስተዋልነው ጌታችን፥ “የጥፋት ርኵሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታይ አንባቢው ያስተውል፥” ብሎ የጠቀሰው ነቢዩ ዳንኤል በትንቢቱ በራዕይ ስላየው ምሥጢር ከትናገረው ክፍል የተወሰደ ነው። ዳንኤል ያየው ራእይ በሱ ዘመንና ከእሱ በኋላም ስለሚደርሰው ጥፋት በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ስለሚደርሰው የአሕዛብ ሥርዓት (የኢጲፋንዮስን ርኩሰት) እና በኋላም በቤተክርስቲያንና በክርስቲያኖች ሕይወት ላይ ስለሚደርሰው ጥፋት የሚያመለክት ነው። (ዳን.11፥31)

ጌታታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ነገር ዳግም ምጽአት ለደቀመዛሙርቱ ከነገራቸው አመልካች ነገሮች ሌላም ነገር ነግሮአቸዋል፦ 1ኛ) “በዚያን ጊዜ እንሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም በዚያ አለ ቢኋችሁ አትመኑ። 2ኛ) እንሆ ሐሰተኛ ክርስቶሶችና (መሲሖችና) ሐሰተኛ ነቢያት ይነሳሉና፥ እነሱ, ቢቻላቸውስ የተመረጡትን (እውነተኞችን ክርስቲያኖች እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክቶችንና ድንቅ ነገሮችን (የምትሐት ድርጊቶችን) ያሳያሉ። 3ኛ) ስለዚህም እነሆ ክርስቶስ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ ወይም በአልፍኝ ነው (በሳሎን ነው) ቢሉአችሁ አትመኑ። 4ኛ) ነገር ግን መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የክርስቶስ (የሰው ልጅ) መምጣትም እንደዚሁ ይሆናል፥” ብሎ ገልጾላቸው ነበር። (ማቴ.24፥23-28)

ዘመናችን ልዩ ልዩ የሃይማኖት ድርጅት የበዛበት እንደሆነ ሁላችንም እናውቃለን። “በጂሆባ ስም የሚታወቀው ክርስቲያን መሰል የሃይማኖት ድርጅት “እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን በሚል የድርጅቱ መጽሐፍ እንደ ገለጸው፥ “ክርስቶስ በ1918-1945 ዓመተ ምሕረት ባሉበት ዓመታት ወደዚህ ዓለም መጥቶአል፤ መምጣቱና ማለቱም በመንፈስ ነው። የጂሆባውያን ግን ዘወትር ይገልጽላቸዋል” ተብሎ ተጽፎአል፤ ይህን የመሰለና ይህም አባባል በወንጌል ዓይን ሲታይ የባልቴቶች ተረት ከመሆን አያልፍም። የክርስቶስ መምጣት ግን ከፍ ብለን እንደ ጠቀስነው ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣው በገሐድ፥ በይፋ፥ በሚያስፈራና በሚያብረከርክ ግርማ ነው።

ቃሉም እንዲህ ይላል፦ “ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፤ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣል። በዚያን ጊዜ የሰው ልጅ ክርስቶስ ምልክት በሰማይ ይታያል። በዚያን ጊዜ የምድር ወገኖች (ሕዝቦች) ሁሉ ዋይ፥ ዋይ ይላሉ። የሰው ልጅም (ክርስቶስም) በታላቅ ኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል። መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል። ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት (መዓዝናት) ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ። (ማቴ.24፥29)

መድኃኒታችንና አምላካችን ለፍርድ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱ በፊት ብዙ ነገሮች እንደሚደረጉ ቢነግረንም እሱ በየትኛው ዓመት፥ በየትኛው ወር፥ በየትኛውም ቀን እንደ ሚመጣ ከእሱ በቀር ፍጡራን የሆኑ ሁሉ አያውቁም፤ ለማወቅም አይችሉም። ለዚያች ቀን እርሱ የተናገረውን እንመልከት፦ “ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም። ጊዜው መቼ እንደሆነ አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፤ ጸልዩም …ማታም ቢሆን፥ ወይም በእኩለ ሌልት ወይም ዶሮ ሲጮኽ፤ ወይም በማለዳ ባለቤቱ መቼ እንደሚመጣ አታውቁምና፤ ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ። ስለዚህ ትጉ፤ ለእናንተም የምነግራችሁን ለሁሉ እላለሁ ትጉ።” (ማር.13፥32-37)

እስካሁን የተመለከትነው ጌታችን የነገረ ምጽአቱን ሁኔታ ለጠየቁት ለደቀመዛሙርቱ የነገራቸው ትምህርትም ማስጠንቀቂያም ነው። ጌታ ከመምጣቱ በፊት ይደረጋሉ ብሎ የተናገረው ከዘመናችን በፊትና በዘመናችንም እየተደረጉ ናቸው። ችግሩና መከራውም በቃሉ መሠረት የሚቀጥል ነው። መድኃኔዓለም እስከሚመጣ ድረስ ይመጣሉ። ነገር ግን ያንጊዜ ለደቀመዛሙርቱ፥ “ተጠንቀቁ፥ ተጠበቁ፥ ትጉና ዘወትር ጸልዩ፥” እንዳላቸው ዛሬም ለእኛ እኮ እየነገረን ነው። በአገልጋዮቹ አንደበት፥ በመጻሕፍት ምሥጢራት እየነገረን ነው።

በእየጊዜው ሐሰተኛ ሰባኪያን በክርስቶስ ስም እኛ ክርስቶሶች ነን እያሉም በእየጊዜው መጥተዋል። እኛ ታዲያ ከእነሱ ራሳችንን ጠብቀናል ወይ? በመካከላችን ያለውን ፍቅር የሚያቀዘቅዙ፥ ቤተሰብንና ቤተሰብን የሚለያዩ (መስሕታን የሚያሳስቱ) በሐሰትና በማስመሰል የሐሰት ትንቢትን

**በመናገር እንዲያስቱን በእጅጉ መጠንቀቅ አለብን። በእምነታችን ጸንተ እንቁም፥ "እስከ መጨረሻው የሚጸና እሱ ይድናል፥" ብሎ ጌታችን የነገረንን ልብ ብለን እንያዘው። ከመድኃኔዓለም የተቀበልናት እምነታችንን አጽንተን እንያዝ። ጌታችን ያስተማረን የሃይማኖታችን መሠረት የሆነውን ፍቅራችን ሰዎችና በሰዎች የሚያድረው ክፉ መንፈስ እንዳይቀዘቅዝብን ክርስቶስን እንልበስ።** (ገላ.3፥27)

**አንድም ሞተ ሥጋም እንደ መጀመሪያው ምጽአታችን ነውና፤ እኛን ለመጥራት በጥዋት ወይም በተሲያት፥ ወይም በማታ፥ ወይም በመንፈቀ ሌሊት ወደ እኛ እንዲመጣ እናውቅምና ተግተን እየጸለይን ተዘጋጅተንም እንጠብቅ።**

**"እስከ መጨረሻው የሚጸና ግን እሱ ይድናል።"**

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**